# ደንብ

**የሞንትጎሞሪካውንቲፐብሊክስኩልስ**

**ተዛማጅ ሠነዶች፡-** ABA-RC, BLB, IGP-RA, IFD-RA, IGT-RA, IIB, ITA-RA
**ኃላፊነት የሚመለከተው ክፍል፡- የትምህርት ክፍል**/Division of Teaching and Learning

## የማስተማሪያ እና የቤተ መፃህፍት ቁሳቁሶች ግምገማ እና ምርጫ

**I.ዓላማ**

መሰረታዊ የትምህርት መርጃ ማስተማሪያ ቁሳቁሶችን እና  የቤተመጻሕፍት ቁሳቁሶችን የመገምገም እና የመምረጥ ሂደቶችን ለመዘርጋት።

ቀደም ሲል የፀደቁ የማስተማሪያ እና የቤተመፃህፍት ቁሳቁሶች MCPS ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ በሜሪላንድ ህግ መሰረት እንደገና የሚገመገምበትን ሂደት ለመዘርጋት።

II. **ትርጉም**

A. በዚህ ደንብ ዓላማ *መብት ያለው ግለሰብ*ማለት በሚከተሉት ሁኔታዎች በቀጥታ እና አሁን ላይ ተጽዕኖ የሚያድርበትን ተማሪ ወክሎ(ላ) የትምህርት ውሳኔዎችን የመወሰን መብት ያለው/ያላት ብቁ ተማሪ ወይም ወላጅ/አሳዳጊ ማለት ነው—

1. ተማሪው(ዋ) በአሁኑ ጊዜ በተመዘገበ(ች)በት ክፍል ውስጥ የተወሰኑ መሰረታዊ ወይም ተጨማሪ የትምህርት መርጃና ማስተማሪያ ቁሳቁሶችን መጠቀም፣ ወይም

2. በአሁኑ ጊዜ በተማሪው(ዋ) ትምህርት ቤት ወይም በክፍል ቤተ-መጽሐፍት ውስጥ ለተማሪዎች ተደራሽ የሆኑ ቁሳቁሶች።

B. *መሰረታዊ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች*ማለት MCPS *ሥርዓተ ትምህርት ጋር* በቀጥታ የተጣጣሙ እና በአንድ ኮርስ ወይም ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ በተወሰነ የትምህርት ኮርስ ወይም ዩኒት ውስጥ ለተማሪዎች እንደ ዋና የትምህርት ምንጭ ሆነው እንዲያገለግሉ የተዘጋጁ ቁሳቁሶች ናቸው።

C. *የቤተ መጻህፍት ቁሳቁሶች* MCPS ደንብ ITA-RA *መሠረት የትምህርት ቤት ቤተ መጻህፍትና ሚዲያ ፕሮግራሞች ሥነ-ጽሑፍን በማድነቅ እና ለትምህርታዊ ስኬት እና ለግላዊ ደስታ ንባብን እና ምርምርን/ጥናትን ለማዳበር የታለሙ የምንባብ ቁሳቁሶች ናቸው። የቤተ መፃህፍት ቁሳቁሶች በት/ቤት እና በመማሪያ ክፍል ውስጥ ያሉትን ቤተ-መጻሕፍት ያካትታል። ለትምህርት መስጫነት ጥቅም ላይ የዋሉ ማናቸውም የቤተ-መጽሐፍት ቁሳቁሶች እንደ ማስተማሪያ ቁሳቁስ መገምገም አለባቸው።*

D. *ተጨማሪ የትምህርት መርጃና የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ትምህርትን ለማስፋት ወይም ለመደገፍ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ቁሳቁሶች ናቸው።*

III **የአሰራር ሂደቶች**

A. አጠቃላይ - የማስተማሪያ እና የቤተ መጻህፍት ቁሳቁሶች አመራረጥ

1. *የትምህርት ክፍል/*The Division of Teaching and Learning (DTL)/ *የግምገማ እና የምርጫ ክፍል የሁሉንም መሰረታዊ እና ተጨማሪ የትምህርት መርጃና የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን (በሌላ መልኩ ካልተገለጸ በስተቀር ከዚህ በኋላ "የማስተማሪያ ቁሳቁሶች" የሚባሉት) እና የቤተ መፃህፍት ቁሳቁሶችን ግምገማ እና ምዘና አስመልክቶ የአሰራር ሂደቶችን ያዘጋጃል/ያስቀምጣል እና ለሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ* (MCPS) *ቢሮዎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ እና ፕሮግራሞች መመሪያ ይሰጣል።*

2. *ለሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ* (MCPS) *ተማሪዎች ጥቅም ላይ ለማዋል የታሰቡ በልገሳ የተገኙ ቁሳቁሶችን ጨምሮ፣ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች እና የቤተ መጻህፍት ቁሳቁሶች ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት፣እንደአግባብነቱ አስተማሪዎችን፣ የትምህርት ይዘት ባለሙያዎችን፣ የትምህርት ቤት ቤተ መጻህፍት ሚዲያ ባለሙያዎችን፣ የእያንዳንዱ ትምህርት ዘርፍ አስተባባሪን/ተቆጣጣሪን፣ እና/ወይም በዋናው የአካዳሚክ ኦፊሰር/ተወካይ የተሰየሙ ሌሎች ሰራተኞችን በሚያካትት የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ* (MCPS) *ባለሙያ ሰራተኞች መገምገም እና መመረጥ አለባቸው።*

3. *መሰረታዊ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች በጊዜያዊነት ለ* 30 *ቀናት የሚፈቀዱ ሲሆን በዚህ ጊዜ ሰራተኞች፣ ተማሪዎች፣ እና አግባብነት ያላቸው ተማሪዎች*

ወላጆች/አሳዳጊዎች በግምገማ እና በምርጫ ዩኒት/Evaluation and Selection Unit ቁሳቁሶቹን መመርመር እና አስተያየት መስጠት ይችላሉ። አስተያየቶች MCPS ቅጽ 281-15፣ MCPS Review of 30-Day Shelf integral Instructional Materials በመጠቀም ሊቀርቡ ይችላሉ። የሚሰጡት አስተያየቶች በሚመለከተው የትምህርት ዘርፍ አስተባባሪ/ሱፐርቫይዘር ይገመገማሉ።

B. ቁሳቁሶችን መለየት

1. ሻጮች/አሳታሚዎች የቁሳቁስ ሽያጭን በተመለከተ በቀጥታ መነጋገር የሚችሉት ከትምህርት ቤት ሰራተኞች ጋር ሳይሆን ከግምገማ እና ምርጫ ክፍል ጋር ብቻ ነው። (በተጨማሪ MCPS ደንብ ABA-RC*በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ወይም በአቅራቢያ የሚገኙ ቬንደሮች*ይመልከቱ)። የቁሳቁስ ሽያጭን ለመጠየቅ ሌሎች ሰራተኞችን የሚያነጋግሩ ሻጮች/አሳታሚዎች ወደ ግምገማ እና ምርጫ ክፍል መመራት አለባቸው።

2. የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ፈቃድ ያላቸው ሰራተኞች ኮንፈረንሶች፣ የሙያ ትምህርት እድሎች እና የትምህርት ቤት ቤተ መጻሕፍት ጆርናሎች በመሳሰሉ ሙያዊ ተግባሮች አማካኝነት አዳዲስ የታተሙ የማስተማሪያ እና የቤተ መጻሕፍት ቁሳቁሶችን እንዲለዩ ይበረታታሉ።

3. የግምገማ እና ምርጫ ክፍል ፈቃድ ያላቸውን ሰራተኞች በመወከል አዳዲስ የታተሙ እና የተሻሻሉ የማስተማሪያ እና የቤተ-መጻህፍት ቁሳቁሶች የቅድመ እይታ እና የግምገማ ቅጂዎችን ማግኘት ይችላል።

C. የማስተማሪያ እና የቤተ መፃህፍት ቁሳቁሶች ግምገማ

የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት/The Maryland State Department of Education (MSDE) በሜሪላንድ ደንቦች ኮድ/Code of Maryland Regulations (COMAR), 13A.01.06.03 *የትምህርት ሚዛናዊነት*ላይ በተቀመጠው እና በሞንትጎምሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA፣ *አድሎ የሌለበት፣ ሚዛናዊነት/ፍትሃዊነት፣ እና የዳበረ ባህል* ላይ እንደተደነገገው ትምህርት ቤቶች የማስተማሪያ እና የቤተ-መጻህፍት ቁሳቁሶችን ለመገምገም ፍትሃዊነትን እና ሚዛናዊነትን እንዲጠቀሙ ይደነግጋል።

1. የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ግምገማ

a) መሰረታዊ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች የተወሰነ ኮርስ ወይም ስርዓተ ትምህርት በሚሰጡ በሁሉም ትምህርት ቤቶች ወይም ፕሮግራሞች ለዲስትሪክት አቀፍ ጥቅም እንዲውሉ MCPS ቅጽ 365-25, *የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ግምገማ ሪከርድ* በመጠቀም በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የትምህርት ባለሙያ ሰራተኞች የትምህርት ዘርፍ ግምገማ እና ምርጫ ኮሚቴ መገምገም እና መመረጥ አለባቸው።

b) ተጨማሪ የትምህርት መርጃ ማስተማሪያ ቁሳቁሶች MCPS ቅጽ 365-25 *የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ግምገማ መዝገብን* በመጠቀም በትምህርት ይዘት ዘርፉ ላይ ያለ አስተማሪን ጨምሮ ቢያንስ በሁለት ፈቃድ ባላቸው ሰራተኞች መገምገም አለባቸው።

c) የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ለአጠቃላይ MCPS ፕሮግራም አወንታዊ አስተዋፅዖ የሚያደርጉ እና በቀጥታ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስርአተ ትምህርት ጋር መጣጣም አለባቸው።

d) በሁሉም የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ግምገማ ላይ የሚተገበሩ መመዘኛዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

(1) ቁሳቁሶቹ በቀጥታ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሥርዓተ ትምህርት ጋር የሚጣጣሙ መሆን አለባቸው።

(2) ቁሳቁሶቹ በርካታ ባህል ካላቸው ማህበረሰቦች እና ከዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ጋር የሚገናኙ እና ያንን የሚያንጸባርቁ መሆን አለባቸው።

(3) ቁሳቁሶቹ የትክክለኛነት ከፍተኛ የጥራት ደረጃዎችን ማሟላት እና የተዛቡ አመለካከቶችን፣ የተዛቡ/የተጋነኑ ማሳያዎችን፣ ፀያፍ ምሳሌዎችን እና የአነጋገር ዘዬዎችን (ከታሪካዊ አገላለፅ ወይም ስነጽሑፋዊ ዓውዶች/ሁኔታዎች በስተቀር) ማስወገድ አለባቸው። ነገር ግን፣ ይህ ክልከላ ከቦርድ ፖሊሲ ACA *መድልዎ የሌለበት፣ ፍትሃዊነት፣ እና የባህል ብቃት ጋር በሚጣጣም መልኩ ለትምህርታዊ ዓላማ እንደዚህ ያሉ ቋንቋዎችን፣ ምስሎችን፣ ወይም ምልክቶችን ሃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ መወያየትን ለመከላከል ጥቅም ላይ አይውልም።*

(4) ቁሳቁሶቹ በአግባቡ ተማሪዎች ማህበራዊ ጉዳዮችን እንዲመረምሩ፣ እንዲተነትኑ፣ እና እንዲገመግሙ እድል ይሰጣቸዋል።

(5) የማስተማሪያ ቁሳቁሶች የሚከተሉትን ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡

(a) የዕድሜ/የክፍል ደረጃ አግባብነትን በማመጣጠን (Motion Picture Movie Association ሲተገበር የዕድሜ ደረጃዎች ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው)

(b) ጊዜው ያላለፈ/የቅርብ ጊዜ መሆኑ – የቅጂ መብት ቀን

(c) ግልጽነት እና ለመረዳት የማያስቸግር

2. የአጠቃላይ የጤና ትምህርት ፕሮግራም ቁሳቁሶች ግምገማ

MSDE አጠቃላይ የጤና ትምህርት ስርአተ ትምህርት የቤተሰብ ህይወት እና ሰብአዊ የጾታ ግንኙነትን የሚመለከቱ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችበስቴት ህግ እና MCPS ደንብ IGP-RA *አጠቃላይ የጤና ትምህርት መማሪያ ፕሮግራም መርኀ መሠረት ተገምግመው ጸድቀዋል።*

3. የቤተ መፃህፍት ቁሳቁሶች ግምገማ

a) ሁሉም የቤተ መፃህፍት ቁሳቁሶች ግምገማዎች ቁልፍ መስፈርቶች ግምት ውስጥ መግባታቸውን ለማረጋገጥ እና እንደአስፈላጊነቱ ደጋፊ ሰነዶችን ለማቅረብ "Database of Accountable Evaluations (DAE)" ይጠቀማሉ።

b) የቤተ-መጻህፍት ቁሳቁሶችን ገምግሞ ለማጽደቅ ከሚከተሉት አንዱ ያስፈልጋል፡

(1) አንድ የትምህርት ቤት ቤተ መጻሕፍት የሚዲያ ባለሙያ እና MSDE የሙያ ፈቃድ ያለው/ያላት (በተለምዶ የትምህርት ቤት ቤተ መጻህፍት ሚዲያ ባለሙያ) የአንድ ተጨማሪ ሰራተኛ ግምገማ እና የማፅደቂያ ፊርማ፣ ወይም

(2) ከአንድ የተመደበ የትምህርት ቤት ቤተ መጻሕፍት ጆርናል ላይ እንደ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የማረጋገጫ ምንጭ የሚያገለግል ሙያዊ ግምገማ የሚያቀርብ አንድ የትምህርት ቤት ቤተ መጻህፍት የሚዲያ ባለሙያ።

b) አዲስ የትምህርት ቤት ቤተመፃህፍት ቁሳቁሶችን በሚገመግሙበት ጊዜ የሚከተሉት መመዘኛዎች ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው:-

(1) ሥርዓተ ትምህርቱን የሚደግፉ እና የሚያበለጽጉ መሆናቸውን

(2) የተማሪዎችን ግላዊ ሁኔታ እና የትምህርት ፍላጎት እንደሚደግፉ

(3) በተለያየ የስነ-ጽሁፍ አቀራረብ ትክክለኛነትን፣ ስነጥበባዊ እና የጥራት ደረጃዎች መሥፈርትን የሚያሟላ መሆኑ መረጋገጥ አለበት።

c) በግምገማ እና በምርጫ ሂደት ለተወሰኑ አጠቃቀሞች ብቻ እስካልተመደቡ ድረስ፥ ሁሉም ተማሪዎች ለነጻ ምርጫ ወይም ለግል ንባብ ወይም ጥናት መምረጥ ይፈቀድላቸዋል። የቤተ መፃህፍት ቁሳቁሶች ደራሲያንን፣ ዘውጎችን ወይም ሌሎች የስነ-ጽሑፍ ፕሮግራምን ለማሳደግ እንደ አንባቢ ድምጽ ሊያገለግሉ ይችላሉ።

D. ቀደም ሲል የጸደቁ የማስተማሪያ እና የቤተ መጻህፍት ቁሳቁሶች ግምገማ

1. የትምህርት ዲፓርትመንት የትምህርት ይዘት ባለሙያዎች እና የት/ቤት ሰራተኞች በስርዓተ ትምህርት ዓላማዎች እና ክለሳዎች፣ በትምህርት ቁሳቁስ የጊዜ ገደብ፣ አሁን ላይ የማይታተሙ/የማይሸጡ የህትመት ስራዎች፣ትክክለኛነት/እውነተኛነት ላይ ያሉ ተግዳሮቶች፣ እና በንፅፅራዊ የገበያ ዋጋዎቻቸው ላይ በመመሥረት በትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ ሁሉንም የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ቀጣይነት ባለው መልኩ ይገመግማሉ።

2. እያንዳንዱ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የትምህርት ቤት ቤተ-መፃህፍት የሚዲያ ባለሙያ ከሌሎች ፈቃድ ካላቸው ሰራተኞች ጋር በመሆን የትምህርት ቤታቸውን የሚዲያ ማእከል የቁሳቁሶች ስብስብ ቀጣይነት ባለው መልኩ ይገመግማሉ።

E. ቀደም ሲል ስለጸደቁት መሰረታዊ እና ተጨማሪ የትምህርት መርጃና ማስተማሪያ ቁሳቁሶች እና የቤተመጻሕፍት ቁሳቁሶችን አስመልክቶ ያሉ ስጋቶችን ስለመፍታት

1. መብት ያላቸው ግለሰቦች በየትምህርት ቤቶቻቸው ጥቅም ላይ የሚውሉ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ወይም የቤተመጻሕፍት ቁሳቁሶችን አስመልክቶ ያሏቸውን ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች መጀመሪያ እኒዚያን ቁሳቁሶች ለሚጠቀሙ ሰራተኞች (ለምሳሌ፡- ለአስተማሪ ወይም የትምህርት ቤት ቤተ-መፃህፍት የሚዲያ ባለሙያ) ማቅረብ አለባቸው። በመምህሩ ወይም በትምህርት ቤት ቤተመፃህፍት የሚዲያ ባለሙያ ያልተፈቱ ስጋቶች ለትምህርት ቤቱ ርእሰመምህር መቅረብ አለባቸው።

2. ርዕሰ መምህሩ/ተወካዩ የስጋቱን ባህሪ እና የተጠየቀውን መፍትሄ፣ እና በተለይም ስጋቱ የትምህርት ማቴሪያሉ ከተፈቀደለት ዓላማ ውጪ ለሌላ ዓላማ ስለመጠቀም ወይም ስለራሱ ስለማቴትሪያሉ መሆኑን ለመወሰን ውይይት የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት። የግምገማ እና የምርጫ ዩኒቱ ርእሰመምህሩን/ተወካዩን መደገፍ አለባቸው።

   a) የትምህርት ማቴሪያሉ ከተፈቀደለት በተለየ መልኩ ጥቅም ላይ መዋሉ ከተረጋገጠ የግምገማ እና ምርጫ ክፍል አስተባባሪው የተፈቀደውን የቁሳቁስ አጠቃቀም ችግር ለመፍታት በትምህርት ቤት አመራርና ማሻሻያ ክፍል እና/ወይም DTL ውስጥ የሚመለከታቸውን/አግባብነት ያላቸውን ሰራተኞች በመምረጥ ረገድ ርዕሰ መምህሩን ይረዷቸዋል።

   b) ማቴሪያሉ በተፈቀደው መሠረት ጥቅም ላይ መዋሉ ከተረጋገጠ፣ ያለውን ስጋት ለመፍታት ተጨማሪ ድጋፍ ለማግኘት እና ማቴሪያሉ/ማቴሪያሎቹ እንደገና እንዲታዩ ለማድረግ ርዕሰ መምህሩ የዋና የአካደሚክ ኦፊሰሩ ተወካይ የሆነውን የግምገማ እና የምርጫ ክፍልን ያነጋግራል።

3. የማስተማሪያ ቁሳቁስ ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ዳግመኛ ያልተገመገመ ከሆነ፣ አስተባባሪው(ዋ) –

   a) ፋይል ከፍተው እንደአግባብነቱ ጥያቄውን የሚመለከቱ ሁሉንም አስፈላጊ ሰነዶች ከርዕሰ መምህሩ ወይም ከትምህርት ቤት ቤተ መፃህፍት የሚዲያ ባለሙያ በመጠየቅ ስጋቱን ለመፍታት ስላደረጉት ጥረት የሚገልጹ ደብዳቤዎችን እና ማስታወሻዎችን ይገምግሙ።

b) ግለሰቡን በማነጋገር ስጋቱን ትብብር በተሞላበት ውይይት እና ምክንያታዊ በሆኑ የችግር አፈታት ዘዴዎች ለመፍታት ይሞክራሉ፣ እና

c) ከግለሰቡ ጋር ያለውን ግንኙነት እና ስጋቱን ለመፍታት የሚደረጉትን ጥረቶች መዝግቦ መያዝ እና ማቆየት እና በተለይም እርዳታ ለማግኘት ወደ ሌላ መስሪያ ቤት የሚላክ/የሚተላለፍ ማንኛውንም ሪፈራል አስመልክቶ ማስታወሻ ሠነድ መያዝ አለባቸው። ይህ መደበኛ ያልሆነ ሂደት ምንም አይነት ቅጾች ወይም መደበኛ ሰነዶች አያስፈልጉትም።

4. ከግምገማ እና የምርጫ ክፍል አስተባባሪ ዘንድ ውሳኔ ካልተገኘ፣ ግለሰቡ(ቧ) ማቴሪያሉ እንደገና እንዲታይ ሊጠይቅ/ልትጠይቅ ይችላል/ትችላለች። አስተባባሪው(ዋ) MCPS *የማስተማሪያ እና/ወይም የቤተ መጻህፍት ቁሳቁሶች እንደገና እንዲታዩ መጠየቅ፣* የሚለውን MCPS ቅጽ 281-18 መብት ላለው አካል ማቅረብ/መስጠት አለበት።

5. ጥያቄውን የሚያቀርበው ግለሰብ የሚመለከተው አካል ካልሆነ እና መጀመሪያ በትምህርት ቤት ደረጃ መፍትሄ ለማግኘት ካልሞከረ በስተቀር እንደገና እንዲታይ የሚቀርቡ ማናቸውም ጥያቄዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም።

F. የማስተማሪያ እና የቤተ መፃህፍት ቁሳቁሶችን እንደገና ማጤን

1. ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ዳግመኛ የተገመገሙ ማናቸውም ቁሳቁሶች እንደገና አይገመገሙም። የቀድሞው ውሳኔ ይፀናል።

2. በተቃውሞ ምክንያት እየተገመገሙ ያሉ ቁሳቁሶች የግምገማው ሂደት እስኪጠናቀቅ ድረስ ለተማሪዎች እና ለትምህርት ቤት ሰራተኞች ጥቅም ላይ እንዲውል የሜሪላንድ ህግ ይፈቅዳል።

3. ከላይ ሰክሽን E ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟላ በድጋሚ ይታይልኝ የሚል ጥያቄን በተቀበለ 10 የስራ ቀናት ውስጥ የግምገማ እና የምርጫ ክፍል አስተባባሪ –

a) ያቀረቡትን ጥያቄ አስመልክቶ የሚኖሩ ማንኛውንም ጥያቄዎች ለማብራራት እንደገና እንዲታይ ከጠየቀ(ች)ው ግለሰብ ጋር የስብሰባ ቀጠሮ ሊይዝ ይችላል፤ እና

b) ማቴሪያሉን በድጋሚ የሚመረምር/የሚመለከት ጊዜያዊ የትምህርት ዘርፍ ግምገማ እና ምርጫ ኮሚቴ ይሰይማል፣ ኮሚቴው ሥራው የሚያጠናቅቅበትን ቀን ያስቀምጣል ጊዜያዊ የግምገማና አስመራጭ ኮሚቴ ይሰይማል፣ እና የተገመተውን ቀነ ገደብ ለግለሰቡ/ቧ ያሳውቃል።

4. አስተባባሪው(ዋ) –

a) እንደአስፈላጊነቱ የት/ቤት ቤተመፃህፍት የሚዲያ ባለሙያ(ዎች)፣ አስተማሪ(ዎች)፣ ርእሰ መምህር፣ አማካሪ(ዎች)፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አስተባባሪ(ዎች) እና አንድ የህዝብ ሴክተር የቤተ-መጻህፍት ባለሙያን ያካተተ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውጪ ለምሳሌ፡- ከሞንትጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ቤተ መፃህፍት፣ እና/ወይም ሙያዊ ሰራተኞችን ያቀፈ ኮሚቴ ጋር ስብሰባ ያደርጋል።

b) በኮሚቴው የተጠየቀውን ማንኛውንም ተጨማሪ ጥናት ያካሄዳል።

5. ኮሚቴው –

a) የግምገማው ርዕሰ ጉዳይ የሆነውን ቁሳቁስ፣ የቀረበውን ሰነድ፣ እና ኮሚቴው ተገቢ ነው ብሎ ያመነበትን ማንኛውንም ሰነድ ይመረምራል፤ እና

b) ለዋናው የአካዳሚክ ኦፊሰር እና ለሥርዓተ ትምህርት አተገባበር እና ለትምህርት ቤት ድጋፍ ዳይሬክተር ምክረ ሀሳብ ያቀርባል፤ ይህም ኮሚቴው ምክረ ሀሳቡን ያቀረበበትን ምክንያት፣ ያካትታል፣ እንዲገመገም በቀረበው ጥያቄ ላይ የተነሱትን ስጋቶች በቀጥታ እና በግልጽ ይፈታል፣ እና ለምክረ ሀሳባቸው መሰረት የሆኑትን ቁልፍ መረጃዎች በአጭሩ ጠቅለል አድርጎ ያቀርባል።

6. ዋናው የአካዳሚክ ኦፊሰር እና የሥርዓተ ትምህርት አተገባበር እና ለትምህርት ቤት ድጋፍ ዳይሬክተር የኮሚቴውን የውሳኔ ሃሳብ ይገመግማሉ፣ ስለ ማቴሪያሉ ውሳኔ ይሰጣሉ፣ እና ውሳኔያቸውን ለግለሰቡ(ቧ) በጽሁፍ ያሳውቃሉ።

a) ሊሆኑ የሚችሉ ውሳኔዎች የቁሳቁሱን ቀጣይ አጠቃቀም ለማረጋገጥ፣ ስለ ዕቃው ቀጣይ አጠቃቀም የተፈቀዱና የተመረጡ ኮርሶችን ወይም የተማሪዎችን ዕድሜ የሚመጥኑ ሁኔታዎችን ግልጽ ማድረግ፣ ወይም ቁሱ

ጥቅም ላይ እንዳይውል ማድረግን ሊያካትቱ ይችላሉ፥ ነገር ግን በዚህ ብቻ አያበቃም።

b) የሚመለከታቸው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች፣ ርዕሰ መምህር፣ ወይም የት/ቤት ቤተመፃህፍት የሚዲያ ባለሙያን ጨምሮ፣ በድጋሚ እንዲፈተሽ ስለታሰበው ቁሳቁስ እና ስለ ግምገማው ውጤት በጽሁፍ ይነገራቸዋል።

7. ግለሰቡ(ቧ) ውሳኔውን ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ይግባኝ ማለት ይችላል/ትችላለች።

H. ይግባኝ

1. ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የሚቀርብ ይግባኝ

የፍትህዊነት እና የድርጅታዊ እድገት ክፍል/ የተማሪዎች ስነ-ምግባር እና ይግባኞች መሰረታዊ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን እና ተጨማሪ/አጋዥ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን እና የቤተመጻሕፍት ቁሳቁሶችን አስመልክቶ በዋና የአካደሚክ ኦፊሰር የሚተላለፉ ውሳኔዎች ላይ ለሚቀርቡ ይግባኞች የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪን ወክሎ ይሠራል። የዋና አካዳሚክ ኦፊሰር ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ፣ይግባኝ ባዩ ውሳኔውን እንዲያውቅ ከተደረገበት ቀን አንስቶ ባሉት 15 ቀናት ውስጥ የተማሪዎች ስነ-ምግባር እና ይግባኞች ክፍልን ማነጋገር አለበት።

2. በቦርድ ፖሊሲ BLB፣ *ይግባኝ እና የችሎት ሂደትን የሚመለከቱ የአሰራር ህጎች*ላይ እንደተገለጸው ለትምህርት ቦርድ የሚቀርብ ይግባኝ

የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ውሳኔ ለትምህርት ቦርድ ይግባኝ ሊባል ይችላል፣ በቦርድ ፖሊሲ BLB፣ *የይግባኝ እና የችሎት አሰራር ደንቦች*

ተዛማጅ ምንጮች፦ የተብራራ የሜሪላንድ የትምህርት ኮድ፣ አንቀጽ፣ 4-142, 7-106, እና 7-910፣ የሜሪላንድ ደንቦች ኮድ 13A.01.06.03, 13A.05.02.13.H እና M, 13A.06.06; እና 13A.09.10.13.

ስለ ደንቡ ታሪክ፦ የቀድሞው ደንብ ቁጥር 3652፣ ኦክቶበር 16, 1980፣ ኖቬምበር 23, 1999 ተሻሽሏል፣ የወቅቱ የቢሮ ስያሜ ጁን 1, 2000፣ ሴፕተምበር 20, 2005 ተሻሽሏል፣ COMAR ስለማክበር ቴክኒካዊ ማሻሻያ ተደርጓል፣ማርች 29, 2023፣ ሴፕቴምበር 9, 2024 ተሻሽሏል፣ ኖቬምበር 18, 2025 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፣ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል" ። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

በሜሪላንድ ስቴት የሚገኙ የህዝብ ትምህርት ቤቶች እና የህዝብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ት/ቤቶች በሙሉ የሚከተሉትን ህጎች በማክበር እንዲሠሩ የስቴቱ ፖሊሲ/ድንጋጌ ነው፡-

(1)የፌደራል ታይትል VI የዜጎች መብቶች ደንብ 1964፣ እና

(2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-

- (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
- (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
- (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

የግንኙነት መርጃዎች እና የፌደራል፣ የስቴት፣ ወይ የአካባቢ መስፈርቶች በተለያዩ ሕትመቶች መካከል ልዩነት ሊኖራቸው ስለሚችል በዚህኛው ህትመት ላይ የተካተተው የሚፀና መሆኑን ልብ ይበሉ። ወቅታዊ መረጃዎችን ለማግኘት እባክዎን ይህን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination.

| MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*** | MCPS ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ *** |
|---|---|
| Director of Student Conduct and Appeals<br>Division of Equity and Organizational Development<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ |
| Section 504 Coordinator ሰክሽን 504 አስተባባሪ<br>Division of Specialized Support Services, Department of School Counseling<br>850 Hungerford Drive, Room 170, Rockville, MD 20850<br>240-987-8031 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*** | |
| Title IX Coordinator<br>Division of Equity and Organizational Development, Department of Student Conduct and Appeals<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ ማሳወቂያ የተሻሻለውን የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።

**ይህ ማሳወቂያ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር ይጣለጣል።

***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል። U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), 61 Forsyth St. S.W., Suite 19T10, Atlanta, GA 30303, 404-974-9406 and TDD: 800-877-8339, OCR.Atlanta@ed.gov, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ"Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org